# ምትሀተ በርጩማ!

ጉድ ፈላብን ዛሬ፣
በርጩማውም ጠፋ ታዘበኝ ሀገሬ!

ለፈረንጁ ኩርኩም ናላችንን ሰጥተን፣
ምክር ተቀብለን፣
ባደባባይ ውርደት፡ ለጠባቦች ጉጭማ፣ ጎንበስ ደፋው ደርቶ፣
ሀፍረት ተከናንበን፣
ሽብሬም ተረስታ፣ ሁለት መቶ ነፍሳት፣
ጥቅማ ጥቅም ፍለጋ፣ ተረስተው ሰማዕታት፣
ቃሊቲ፣ ዴዴሳ፣ ዝዋይ--ሸዋ ሮቢት፣ የታጎረው ሁሉ፣
ካንጎል ተሰርዞ፣ ስሙ ላይነሳ፣
ትኩረታችን ሆኖ በርጩማ ፍለጋ ።
ክመ እርያ ጭቃ፣ ወያኔ ሸበጥ ስር፣ ወድቆ መንከባለል፣
ከባለጌ መንጋ፣ ውሎች መፈራረም፣
ከጋጠ ወጡ ጋር፣ ስነ ምግባር ማውካት፣
መታለልን መርጠ፣ መንቃትን ግን መፍራት፣
ከሕዝብ ተነጥሎ፣ የሕዝብ ድጋፍ መሻት፣
ክስረት ፖለቲካ፣ የተነኳለለ፣
የውርደት ማቅ አልባሽ፣ ምንም ያልጠቀመ፣
ጉድ ያፈላ ዛሬ፣ በርጩማም ያሳጣ፣
ሰብዕናን ሽጦ ሰው በሉኝ ጫጫታ!

ጉድ ፈላብን ዛሬ፣
በርጩማዋም ጠፋች ታዘበኝ ሀገሬ ።

የደደቢት ውላጅ፣ የወያኔ ውራጅ፣ ቤዛችን ተብሎ፣
በቅዠት ነቢያት፣ የወያኔ ሸንፈት፣
በተምቤን፣ ባድዋ፣ በአቾፈር፣ በጸለምት፣
በይፋ ተነገሮ፣

ከበሮ ሲደለቅ፣ ቃላችን ተብሎ፣
ከምርጫ ሳጥን ውስጥ፣ ታይቶ ድል ሲሰረጽ፣
ታቀቡ ! አደብ ግዙ ! 97ን ከቶም እንዳትረሱ ! ያሉትንም ማውገዝ፣
በወያኔ ህድሞ፣ ተዓምር የጠበቁ፣
ቅሌትን አርግዘው፣ ውርደትን ወለዱ፣
ዛሬማ ጉድ ፈላ፣
ያ ሁሉ ሽብ ረብ፣ ነፍስም ተገበረ፣
ለሁለት በርጩማ!
አንዱ በቃኝ ኣለ፣ ቀሪውም እጅ ሰጠ፣
አይታክቴው አታክቴም፣ ዛሬም እንደ ትላንት እያ ነሆለለ፣
ቅሌትን ለመድገም፣ ኣምስት ዓመት ስጡን፣ እንዘጋጅ አለ፣
ተረግጠ ሊገዛ፣ ትግል እየገደለ።
ብቻውን የበላ፣ ብቻውን ይሞታል፣
ብቸኛ ኣሽናፊ፣ ኣጃቢ ያዋርዳል፣
ወያኔ ሀፍረተ ቢስ፣  የደደቢት ጠባብ፣ መቸ ተለውጦ፣
መች ይሉኝታ ገዝቶ፣ መች ቃሉን ኣክብሮ?
ለዱላው ቢመቹት፣ ልክ እንደ ከበሮ፣
በርጩማ ሊሰጥስ፣ መች ፍንጭ አሳይቶ?
ነግ ጠባ መጃጃል፣  መሳለቂያ መሆን፣ የመረጡን ሁሉ፣
ወያኔ ዘረረ፣ ዳግም ነፍስ ላይዘሩ።
በርጩማ ወልጋዳ፣ ድፉጭ ያለ ነገር፣
የደደቢት ምትሀት እርባና ቢስ ነበር ።

በርጩማውም ጠፉ፣ ቅሌትን ትቶልን፣
በባዶ በከንቱ፣ ስንት ነፍስ ገበርን ?!
ስህተትን በመድገም አሻንጉሊት ሆነን።
በርጩማውም ጠፉ፣ ውርደትንም አቀፍን!

ሀማ ቱማ